ወደ

ኋላ

መመለስ

ወደ ኋላ መመለስ ።

«ዓመጻቸውን እፈውሳለሁ በገዛ ፈቃዴ እወዳቸዋለሁ ።» (ሆሴዕ ፲፬ ፥ ፬) ወደ ኋላ መመለስ ማለት ስለ ጌታ ያለው ስሜት ሲቀዘ ቅዝና ለእርሱ ፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ፥ ለጸሎት ፥ ለቤተ ክርስቲያንና ለመመስከር ያለው ፍላጎት ሲጠፋ ነው ። ወደ ኋላ መመለስ ማለት ከእግ ዚአብሔር ወደ ዓለም መመለስ ማለት ነው ። (፩ኛ ነገሥ. ፲፩ ፥ ፱ ፤ ራእይ ፪ ፥ ፬ ፤ ኢሳ. ፶፱ ፥ ፪)

ክርስቲያኖች ይወድቃሉ አወዳደቃቸ ውም አስፈሪ ነው ። (፩ኛ ቆሮ. ፲ ፥ ፲፪ ፤ ምሳ. ፲፮ ፥ ፲፰) ለረዥም ጊዜ የጸኑ የመሰሉት በድ ንገት ይሰናከላሉ ። ሆኖም ወደ ኋላ መመለስ በድንገት ከእግዚአብሔር መለየት አይደለም ። ብዙ ጥቃቅን ነገሮች ገብተው ለጌታ ሊሆን በሚገባው ነገር ላይ ሠልጥነዋል ። ስለዚህ የሚታየው ውድቀት በድንገት ይሁን እንጂ እውነተኛው ነገር ለሌሎች ስውር ሆኖ ሥር የሰደደና የቆየ ነው ።

በሌላ አባባል ለሌሎች የሚታይ ግልጽ የውድቀት ምልክት ባይኖርም የወደቀው ክር ስቲያን በልቡ የተሳሳተውን ነገር ያውቃል ፥ በሕይወቱ ያለውን ስህተት እንኳ ለማረም ፍላጎት አይኖረውም ይሆናል ። ስለዚህ ነፍሱ እረፍትን ታጣለች ። ከጌታ ጋር የቅርብ ግን ኙነት የሚሰጠውን ነገር ስለናቀ ደስታና ሰላም የለውም ።

በዚህ ሁኔታ ላይ ያለ ምዕመን በጣም ደስታ የራቀውና ጌታን የሚያሳዝን ነው። ሌሎች እንደሚመለከቱት የውድቀት ምክን ያት ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

፩. መጎምጀት። ዘፍ. ፲፫ ፥ ፲

፪. ሰውን መፍራት። ማቴ. ፳፮ ፥ ፫—፭፬

፫. የኩራት መንፈስ። ምሳ. ፲፮ ፥ ፲፰

፬. ራስን መውደድ። ምሳ. ፲፬ ፥ ፲፬

፭. አለመታዘዝ። ፩ኛ ሳሙ. ፲፭ ፥ ፲፩

፮. የገንዘብና የንብረት ፍቅር። ፩ኛ ጢሞ. ፮ ፥ ፱ ፥ ፲

፯. ዓለምን መውደድ። ፪ኛ ጢሞ. ፬ ፥ ፱

የችግሩ ምንጭ ግን የሚገኘው በምዕመኑ ሁኔታ ወይም የክርስቶስን ጌትነት በምን ዓይ ነት እንደተቀበለው ነው። ብዙ ሰዎች የፍጥ ረታት ጌታ፥ የዓለምም ገዥ መሆኑን ያምናሉ የሕይወታቸው ጌታ አድርገው ግን አይቀበሉ ትም። የሕይወቱን ኃላፊነት በእጁ የሚያደ ርግ፥ የክርስቶስን ሥልጣን የሚያክፋፋ፥ የእግ ዚአብሔርን ፈቃድ ሳይጠይቅ በራሱ ውሳኔ የሚመራ፥ ለራሱ ደስታ ብቻ የሚኖር፥ ራሱን ሙሉ በሙሉ ከክርስቶስ ጋር አያመሳስልም።

ስለዚህ እውነተኛው የውድቀት ምክን ያት የሚከተለው ነው።

፩. ለእግዚአብሔር ሙሉ ኃላፊነት አለ መስጠት ሮሜ ፮ ፥ ፲፮።

፪. የእግዚአብሔርን ቃል አለማንበብና አለመጸለይ። ፪ኛ ጢሞ. ፪፥፲፭፤ መዝ. ፻፱ (፻፲፰)፥፲፯

፫. ከሌሎች ምዕመን ጋር አለመገናኘት። ዕብ. ፲፥፳፭

፬. መንፈስ ቅዱስን አለመታዘዝ። ኤፌ. ፬፥፴

፭. ስለ ክርስቶስ ለሌሎች አለመመስከር። ማቴ. ፲፥፴፫

፮. በእግዚአብሔር መንገድ አለመራመድ። ፩ኛ ዮሐ. ፩፥፯

፯. የእግዚአብሔርን መሪነት አለመፈለግ። ዕብ. ፲፪፥፪፤ መዝ. ፴፩(፴፪)፥፰

፰. ኃጢአትን አለመናዘዝ። ፩ኛ ዮሐ. ፩፥፱

ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነቱ የተቋረጠ ምዕመን በሕይወቱ ኃይል፥ ሰላምና ደስታ የለውም። እግዚአብሔር ግን እንዲመለስ ይጠራዋል። «ተመለሱ . . . ዓመጻችሁን እፈውሳለሁ።» (ኤር. ፫፥፲፪) መንፈስ ቅዱስ ውድቀትን ለማሸነፍ ይረዳል። (፩ኛ ዮሐ. ፩፥፱)

ወደ ክርስቶስ መመልከቱን በማያቋርጥ፥ (ዕብ. ፲፪፥፪) ክርስቶስን ግቡ በሚያደርግ፥ (ፊልጵ. ፫፥፲፬) ኃይል የሚሰጠውን አምላክ በሚያመሰግን ምዕመን ላይ ውድቀት የለም። (፩ኛ ጢሞ. ፩፥፲፪) ምዕመንን ከውድቀቱ የሚጠብቅ ክርስቶስ ብቻ ነው። (ይሁዳ ፳፬)

S.I.M. Press